Legacy International Spiritual Ministry

# 2017 Gc Annual Summary Report



**Legacy International Spiritual Ministry**
**P.O.Box 192/1070**
**Cell # 251 930 651943**
**Act: #; Berhan Bank 2600010008458**
**Addis Ababa, Ethiopia**

***ለዉድ የሌጋሲ መንፈሳዊ አገልግሎት ደጋፊዎች!***

***ጉዳዩ፡ የሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት እአአ 2017 ዓመታዊ ሪፖርት በአጭሩ***

ሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት አንደኛ ዓመት ክብረ በዓሉንና ጠቅላላ ጉባዔውን ጥር 2010 ዓም ባደረገበት ወቅት ሪፖርት እንደተደረገው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ዘንድ ብዙም ትኩረት ያልተሰጠውን ትዉልድ ክፍተት በማየት አገልግሎቱን በይፋ ከጀመረ ከጥር 2009 ዓም ጀምሮ የሚከተሉትን ፋና ወጊ ተግባራት በእግዚአብሔር እርዳታ ማከናወን ችሏል፡፡ አገልግሎቱ ራእዩን እውን ለማድረግ በቅድሚያ ‹‹በትንሹ መጀመር›› በሚል የአደረጃጀት መርሆና ‹‹እግዚአብሔርን የማያውቅ ትውልድ እንዳይነሳ›› የሚል አንኳር መልእክት በማንገብ ሥራውን የጀመረው ይህ አገልግሎት የአማካሪ ቦርዱ ትጋት ታይቶበታል፡፡

በዚሁም መሠረት ቦርዱ በበጀት ዓመቱ ዉስጥ አንድ የመቋቋሚያ ስብሰባ፣ ሶስት መደበኛና አንድ ኢመደበኛ ስብሰባዎች ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በእነዚህ ስብሰባዎቹ ቦርዱ በልዩ ልዩ አጀንዳዎች ላይ አመርቂ ውይይት በማድረግ ውሳኔዎችን በማስተላለፉ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ሊደረጉ ችለዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በበጀት ዓመቱ የበጎ ፈቃደኞችን በተለይም የሂሳብ ባለሙያና ካሼር የማፍራትና የመመደብ ሥራ እንዲሁም ቀደም ብሎ በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠው ኦዲተር ሥራውን እንዲያከናውን የማመቻቸት ሥራ ይገኙበታል፡፡

በዓመቱ ውስጥ አገልግሎቱን የማስተዋወቅ፣ ድጋፍ የማሰባሰብ፣ የግንኙነት መረብ የማጠናከር ሥራዎችን አጥጋቢ በሆነ መልኩ የተሠራ ሲሆን በጎ ፈቃደኞች በገንዘባቸው፣ በጊዜያቸው፣ በእውቀታቸውና በሀብታቸው ከዚህ አገልግሎት ጎን ለመቆምና አብሮ ለማገልገል ቃል በገቡት መሠረት አገልግሎቱን ስለደገፉም አመርቂ ውጤት የታየበት ሲሆን ይህም ራእዩን የማስረጽ ውጤት ሆኖ ታይቷል፡፡

**የሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት እአአ 2017 ዓመታዊ ሪፖርት በአጭሩ**

ከዚህም ጋር ተያይዞ ለአገልግሎቱ መነሻ የሚሆን ቢሮ ለአንድ ዓመት በስጦታ በበጎ ፈቃደኛ ቤተሰብ መበርከቱ ለሥራው እንቅስቃሴ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ የአገልግሎቱ አንኳር ማለትም ሥልጠና ለሚመለከታቸዉ ተደራሾች በእቅዱ መሠረት መሰጠቱ አጥጋቢ አርአያነት ያለው ነበር፡፡ በመሆኑም



1ኛ ስለወጣቶች **ተግዳሮቶችና** መፍትሔያቸው እንዲሁም **በአምስት የወጣት ሕይወት መንፈሳዊ ምሰሶዎች** ላይ(**መዳን፣ መመሥረት፣ መግባባት፣ መታደስ፣ መሸከም**) ‹‹በልዩነት የተገለጠ ክርስቲያናዊ ወጣት›› በሚል መሪ ሃሳብ ሥር የወጣትነት ማንነት፣ ግኑኝነት፣ መንፈሳዊ አቋምና ዓላማ ላይ ያተኮረ ሥልጠና አዲስ አባባ ዉስጥ በሚገኙ ሁለት ሙሉ ወንጌል አጥቢያዎች (ቦሌ ቡልቡላ፣ ሳሪስ እርሻ ሰብል) እና በክፍለ ሀገር በሚገኙ ሶስት (ሆሣዕና፣ ኮምቦልቻ፣ ዳንግላ) አጥቢያዎች አስተባበሪነት ለተለያዩ ወንጌላዉያን አብያተ ክርስቲያናት 120 ወጣቶች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

2ኛ ለወላጆች ደግሞ ‹‹እግዚአብሔርን የማያውቅ ትውልድ እንዳይነሳ›› በሚል መሪ ሃሳብ ሥር **በሰባት መንፈሳዊ ምሰሶዎች (ማስተዋል፣ ማዳን፣ ማስመለጥ፣ ማሳየት፣ ማስጠንቀቅ፣ ማስረከብ፣ ማስተላለፍ**) ላይ ያተኮረ በአዲስ አበባ (ሳሪስ እርሻ ሰብል) በክፍለ ሀገር (ሆሣዕና፣ ኮምቦልቻ፣ ዳንግላ) በተለይ በቤት ላይ በማተኮር ከማኅጸን ጀምሮ የልጆች አያያዝን በተመለከተ በምሳሌነት ለትዉልዱ ትኩረት መስጠት እንድችሉ ለ154 ወላጆች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡



3ኛ፣ ‹‹እግዚአብሔርን የማያውቅ ትውልድ እንዳይነሳ›› በሚል መሪ ሃሳብ ሥር በክፍለ ሀገር ለሚገኙ አንድ አጥቢያ ቤ/ክ መሪዎች (ሆሣዕና ቃለ ህይወት) እና ሌሎች ሁለት አጥቢያዎች (ኮምቦልቻ፣ ዳንግላ) አስተባባሪነት ከተለያየ ወንጌላዉያን አብያተ ክርስቲያናት ለተዉጣጡ በድምሩ ለ72 የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለተተኪዉ ትዉልድ ትኩረት እንዲሰጡት **ደወል** የማሰማት ሥራ ተሠርቷል፡፡



በዘሁም መሠረት በአጠቃላይ 346 ወገኖችን በሥልጠና መድረስ የተቻለ ሲሆን ይህም በበጀት ዓመቱ ለማከናወን ታቅዶ ከነበረው አኃዝ ጋር በመቶኛ ሲነፃጸር በዚህ ዓመት አገልግሎቱ የአጠቃላይ እቅዱን 99 በመቶ ማሳካቱ ይበልጥ ደስ የሚያሰኝ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ሠልጣኞች ባገኙት ትምህርት መጠቀማቸዉን፣ ሌጋሲ እግዚአብሔር በጊዜዉ ያስነሳዉ አገልግሎት መሆኑንም ብዙዎች የተናገሩ ሲሆን ብዙ ወጣቶችም በግል ከጌታ ጋር በመገናኘት መንፈሳዊ ህይወታቸዉን ለማጠናከር በአንደበታቸዉም ሆነ በጽሑፍ ቃል ገብተዋል፡፡

የዓመቱ ሌላው ወርቃማ ዜና አገልግሎቱን በሰው ኃይል ከማደራጀት አንጻር ቦርዱን ጨምሮ 12 ለሚሆኑ ኮር ቲም አባላት የሁለት ቀናት የግንዛቤ ማስጨበጫና የምክክር ጊዜ በደብረ ዘይት መካሄዱ ነዉ፡፡ በዚህም ጊዜ በአገልግሎቱ ዉስጥ በንዑስ ዓላማ በተካተቱ አንኳር አምስት ጽንሰ ሀሳቦች (መሪነት ማጎልበት፣ ሥራ ባህል፣ ትዉልድ ተንከባካቢነት፣ ክርስትና እሴት፣ ሚዲያ) ላይ አምስት ተናጋሪዎች በተለያዩ ርዕሶች ላይ ከእግዚአብሔር ቃል አንፃር አካፍለዋል፡፡ አባላቱ በጊዜው ንቁ ተሳትፎ የነበራቸው ሲሆን ትውልዱን በተመለከተ በቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮችም መነካታቸውንና በዚህ አገልግሎት በቀጣይነት በትጋት የየበኩላቸዉን አስተዋጽኦ በማድረግ እንደሚቀጥሉ ያላቸውን ፈቃደኛነት የገለጹበት ነበር፡፡

እአአ 2017 (ጃኑዋሪ እስከ ዲሴምበር) ለዓመቱ ተይዞ የነበረው በጀት ብር 840,175 ሲሆን የተሰበሰበዉ ገቢ ብር 143,137.11፤ አጠቃላይ ወጪ ብር 93,421.20፤ ከወጪ ቀሪ ደግሞ ብር 49,715.91 መሆኑ በኦዲተር ተረጋግጦ ለጠቅላላ ጉባዔ ሪፖርት ተደርጎ ተቀባይነት አግኝቶ በቀጣይነት ግን የጥሪት ማሰባሰብ ሥራዉ ተጠናክሮ በትኩረት እንዲከናወን ማሳሰቢያ ተሰጥቶበታል፡፡

በማጠቃለያም አገልግሎቱ በእግሩ እንዲቆም በትጋት ለተንቀሳቀሱ መሥራች አባላት፣ አገልግሎቱ ቅርጽ እንዲያገኝ ከፍተኛ ሚና ለተጫወቱ የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባዔ አባላትና አሁንም እየሠሩ ላሉ፣ በበጎ ፈቃደኝነት እያገለገሉ ላሉ፣ ጥሪታቸዉን በማካፈል ላይ ላሉ ግለሰቦች (በሀገርና ዉጭ ለሚገኙ) እንዲሁም በተለይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረገች በሳንዲያጎ ላለች ቤተ ክርስቲያን፣ ቢሮ ስለሰጡ ቤተሰብ፣ በራቸዉን በመክፈት በትብብር እየሠሩ ላሉ (አአ ዉስጥ፣ ከአአ ዉጭ) አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ወጣቶች፣ ወጣቶች ከአባቶችና እናቶች ለመስማት ስላሳዩት ይሁንታ፣ ኤስ አይ ኤም ስብሰባ በሚኖረን ጊዜ ሁሉ ቦታ ስለፈቀደልን፣ ለፌዴራል መንግሥት ፈቃድ ሰጥቶ መንቀሳቀስ እንዲቻል ስላደረገ፣ ቦርዱ በትጋት ስለመራ፣ ጥልቅ ምስጋናና ዕዉቅና በመስጠት ሪፖርቱ ተጠናቋል፡፡

እአአ 2018 ዓም ለአገልግሎቱ ብር **840,280** በጀት በጠቅላላ ጉባዔ ጸድቋል፣ ቀጣዩም ሥራ ተመሳሳይና ሚዲያን የሚጨምር ነዉ፡፡ በጉባዔዉ መጨረሻ አዳዲስ አባላትን የመቀበልና የጎደሉ ሁለት የቦርድ አባላትን የመተካት ሥራ ተከናዉኗል፡፡ በተጨማሪም የ2017 አገልግሎት ሂደት እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ፎቶግራፎች በመጎብኘት ጉባዔውና 1ኛ ዓመት ክብረ በዓሉ ተጠናቋል፣ ዜናዉም በኤልሻዳይ ቴሌ ቪዥን ተላልፏል፡፡

***ለዚህ አገልግሎት መሳካት የበኩሎዎን ድርሻ ስላበረከቱ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክዎ፡፡***

***ተፈጸመ***

ለአገልግሎቱ እአአ 2018 ዓመት ብር **840,280** በጀት ቀርቦ በጠቅላላ ጉባዔ ጸድቋል፤ ከዚህም በተጨማሪ አዳዲስ አባላትን በመቀበልና የጎደሉ ሁለት የቦርድ አባላትን በመምረጥና በመተካት የ2017 የአገልግሎቱን ሂደት እንቅሰቃሴ የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ፎቶዎችን በመጎብኘት ጉባዔውና አንደኛ ዓመት ክብረ በዓሉ ተጠናቋል፣ ዜናዉም በኤልሻዳይ ቴሌ ቪዥን እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡